የሰ/መ/ቁ. 60025

ግንቦት 2 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ መልድ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ነገረፈጅ ተስፋዬ ከርጋ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች**፡-1. አቶ ወልዱ በየነ ቀረቡ፡፡

2. አቶ ታምሩ አያለው - ቀረቡ፡፡

3. አቶ አየለ ዋቀዮ
4. አቶ ተስፋዬ በዳዳ
} በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ተወካይነት ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የደሞዝ ጨማሪን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በበታች ፍ/ቤት ከሣሾችና አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱ የቀረበው በኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግሥት የምሥረቅ ኦሮሚያ አሰሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን ቀርቦ የነበረው ክስ በጡረታ እድሜያችን የጡረታ አበል ያገኙ የነበረና ተከሣሽ በኮንትራት ሲቀጥረን በጡረታ በምናገኘው ክፍያ ላይ 291 ብር ጨምሮ ይከፍለን የነበረና የጡረታ ደብተራችንም የተመለሰ መሆኑ ይሁን እንጂ የጡረታ እና ዋስትና ባለሥልጣን ከሐምሌ 1999 ዓ.ም ጀምሮ ጭማሪ ቢያደርግም የአሁን ተከሣሽ በደሞዛችን ላይ እንዲጨምርልን ስንጠይቅ መልስ ሣይሠጠን ቆይቶ ከጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ ግንቦት 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን ብቻ ከፍሎናል፡፡ ስለዚህ ከሐምሌ 1 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ18 ወር ውዝፍ እንዲከፍል የሚል ነበር፡፡

ተከሣሽ በበኩሉ በሠጠው ክሣሾች በጡረታ ላይ የነበሩ ቢሆንም በግልፅ ውል በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 4 መሠረት ተቀጥረው እንደማንኛውም ሠራተኛ የሚመለከታቸውን ደሞዝና ጥቅማጥቅም እያገኙ ነው፣ ማህበርዊ ዋስትና በኑሮ ውድነት ምክንያት ደሞዝ ሲጨምር እኛም መጨመር እንዳለብን የተደረገ ስምምነት የለም፡፡ እንዲሁም ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆናል በማለት ተከራክሯል፡፡

ቦርዱ ከላይ እንደተመለከተው ከክርክር በኂላ የቀረበው ክስ የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁን ተጠሪዎች ቅር በመሠኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብለው ፍ/ቤቱ ከክርክር በኂላ የአሁን አመልካች ከሐምሌ 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ መንግሥት በጨመረው መሠረት ለአሁን ተጠሪዎች ሊከፍላቸው ይገባል በማለት የቦርዱን ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ ከዚሁ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሲሆን በ03/13/2003 2 ገጽ በተፃፈ አቤቱታ መንግሥት የሰጠውን ጭማሪ አስቀምጦ በውላችን ውስጥ የካተተ ነገር ባለመኖሩ ልንከፍል አየገባም፡፡ በተጨማሪም ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት አመልክቷል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በ29/03/2003 ዓ.ም 2 ገጽ ላይ ጽፈው ባቀረቡት መልስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ በመሆኑ እንድፀና የሚል ነበር፡፡ ከዚህ በኂላ አመልካች የመልስ መልስ እንድያቀርብ በተቀጠረበት ባለመቅረቡ መዝገቡ ለምርመራ አድሯል፡፡

በግራ ቀኙ የተደረገው የክርክር ሂደቶች ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረበውን ቅሬታ ከተያዘው ጭብጥና ከሚመለከታቸው ሕጎች ጋር መርምሮአል፡፡ እንደመረመርነውም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል የክፍያውን አግባብነት በግራ ቀኙ መካከል ከተመሠረተው የሥራ ውል አኳያ ለመመርመር ነው፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን ከዚህ አኳያ መርምሮታል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የአሁን ተጠሪዎች በጡረታ ላይ የነበሩ ሰዎች ሆነው የቅጥር ውል ከአሁን አመልካች ጋር የፈፀሙ ስለመናቸው አላከራከረም፡፡ ይሄ የሥራ ውል ግንኙነት በመፈጠሩ ምክንያት የጡረታ ደብተራቸውን ለሚመለከተው የመንግሥት አካል የመለሱ መሆናቸውን ተጠሪዎች ራሣቸው አመልክተዋል፡፡ በግራ ቀኙ የሥራ ውል ውስጥ አመልካች ለአሁን ክስ ምክንያት የሆነውን ክፍያ ለመክፈል የገባው ግዴታ ያለመኖሩን አመልካች የተከራከረ ሲሆን ተጠሪዎችም በውላቸው ውስጥ የተቀመጠ ግዴታ ስለመኖሩ ያነሱት ነገር ካለመኖሩም በላይ እንደዚህ ዓይነት ግዴታ በመካከላቸው ያለመኖሩን የበታች ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል አንድ ጡረታ የወጣ ሰው ተመልሶ ብቀጠር እንደማንኛውም ተቀጣሪ ሠራተኛ ማግኘት ያለበትን ክፍያ ከመጠየቅ ባለፈ ለጡረተኞች የክፍያ ጭማሪ በማደረጉ ብቻ አመልካች የተደረገውን ጭማሪ እንድከፍል የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች መንግሥት ለጡረተኞች ያደረገውን የደመወዝ ጭማሪ ለተጠሪዎች እንዲከፍል በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/93661 በ29/10/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምሥራቅ ኦሮሚያ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በቁጥር 664/01/2002 በ26/6/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች ጡረታኝነታቸውን በመተው የሥራ ቅጥር ውል ከአመልካች ጋር ከፈፀሙ በኂላ መንግሥት ለጡረተኞች በኑሮ ውድነት ምክንያት ደሞዝ ጨምሯል በሚል አመልካች ጭማሪውን እንዲከፍል ለመጠየቅ የሚያስችል ከውል ወይም ከህግ የሚመነጭ መብት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ላይ የደረሰውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልስናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ